# በአጠቃላይ አስተያየት የማይደበቁ እውነታዎች

ዘስላሰ ግደይ

ከትግራይ ህዝብና መንግስት ግኑኝነት ቢሮ

በትግራይና በሀገራችን የተጀመረው የመልካም አስተዳደር ንቅናቄ አስመልክቶ ያለውን ለውጥ በተከታታይ በዓይጋ ፎረም ሲወጡ እነሱን ተከትሎ የተለያዩ መከራከርያ ነጥብ በማንሳት መሟገት የተለመደ እየሆነ መጥቷል። በተለይም ሂደቱ እያለፈባቸው የሚገኙ ፈተናዎችን መሰረት በማድረግ የሚካሄዱ ክርክሮች ጎላ ብለው ይታያሉ።

ከነዚህ መካከል በቅርቡ ያጋጠሙ ችግሮች በመነሻነት በመጠቀም በዓይጋ ፎረም አንዳንድ ፀሃፊዎች በአጠቃላይ አስተያየት ያለፍዋቸው እውነታዎች ገለጥለጥ አድርጎ ለአንባቢ ማቅረብ ተገቢ ነው። ሰሞኑን ካነበብኳቸው ፅሁፎች መካከል 'በትግራይ የክልሉ ተወላጆች ሃብታቸውንና እውቀታቸውን ተጠቅመው ለማልማት ሲፈልጉ ሁኔታዎች ምቹ አይደሉም። ዋናው ጉዳይ ግን ህወሃትና የክልሉ መስተዳድር እንዴት አድርገን ነው መግፋቱን ትተን መሳብ የምንችለው ብሎ ሌት ተቀን መጨነቅ አለበት።' የሚለው መገላለጥ ከሚያስፈልገው አጠቃላይ አስተያየት አንዱ ነው። የት? ማን ተገፋ? መቼ? የሚል ብቻል ማስረጃ ባይቻል መረጃ አገኝበታሎህ ብየ እነዚህን ፅሁፎች በተለይም የጀነራል ፃድቃን ፅሁፍ ጊዜ ወስጄ ባነበውም እንዳልኩት አጠቃላይ አስተያየት ሆኖ ስላገኘሁት በዚህ ረገድ በትግራይ ያለው እውነታ ከአሁን ቀደም ከተፃፉት ውጭ በቅርቡ ያሉት እውነታዎች እንደሚከተለው ላቅርብ ።

በዚህች ሳምንት ብቻ እንኳን የክልሉ ካቢኔ የኢኮኖሚ አዋጭነት እንዳላቸው ታምኖባቸው ከተለያዩ የክልሉ ከተሞች የተላኩና የሊዝ ፖሊሲው ማበረታቻ ለሚፈቅድላቸው 21 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በመተዎች ከሚቆጠር እስከ 10ሺ ካሬ ሜትር ቦታ ነፃ ሊባል በሚችል የየአከባቢው ሊዝ መነሻ ዋጋ እንዲሰጥ አፅድቋል። ከነዚህ ባለሃብቶች መካከል ሁሉም ሊባል በሚችል መልኩ የክልሉ ተወላጆች ሲሆኑ የተወሰኑት ደግሞ ከተለያየ የሀገሪቱ አከባቢ የመጡና እያንዳንዳቸው እስከ 200 ሚልዮን ብር ካፒታል በባንክ ያላቸው ናቸው። ከነዚህ ፕሮጀክቶች መካከል ትላልቅ ሎጆች፣ ሞቴሎች፣ የአርትና ቱሪዝም ጋሌሪዎች የማኖፋክቸሪንግ ኢንዳስትሪዎች ይገኙበታል።

ሌላው እውነታ ይህ የክልሉ ጥረት ግንባታው በቅርቡ የሚጀመረው የኢንዳስትሪ ፓርክ ውስጥ ገብተው እንዲሰሩ ጥሪ ተደርጎላቸው መመዝገብ የጀመሩ የአገር ውስጥና የውጭ ባለሃብቶች አይጨምርም። የአገር ውስጥ ባለሃብቱ የግብር እፎይታ ግዜ፣ በሊዝ ዝቅተኛ መነሻ ዋጋ መሰረተ ልማት የተሟላለት መሬት የማግኘትና የብድር አቅርቦት ማበረታቻዎችን ያገኛል። ለዚህም ሲባል የመካከለኛ ማኒፋክቸሪንግ ኢንዳስትሪ የሚደግፍ ተቋም በቅርቡ በክልሉ ምክርቤት በተካሄደ ጉባኤ በፀደቀ አዋጅ ተቋቁሟል።

ተመሳሳይ ማበረታቻ አግኝተው እየሰሩ ካሉ የጀነራል ፃድቃንና ጋደኞቻቸው ራያ ቢራ ጨምሮ እስከ አሁን መሬት በሊዝ መነሻ ዋጋ ወስደው ግንባታ ባልጀመሩ ትላልቅ የትራንስፖርት ካምፓኒዎች በተለይም የራያ ቢራ እህት ኩባንያ የሆነው ራዝ 30ሺ ካሬ ሜትር ቦታ የክልሉ ካቢኔ አፅድቆ ከሰጠው ምንያህል ጊዜ ሆነው? ለመገንባት አንድ ሌሊት አናሳድረውም ተብሎ አይደል እንዴ በአጣዳፊ የተሰጠው? ሌሎችም ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች እንዴት እንዳሉ እንነጋገር። ጀነራሉ በራሳቸውና በቅርብ የሚያውቋቸው ጋደኞቻቸው ካምፓኒዎች ያጋጠማቸው ችግር ካለ ቀርቦ በጉዳዩ ላይ ከጥላቻ በራቀ መንፈስ ፍርጥርጥ አድርገን እስኪ እንነጋገር። ይህ ካደረጉ እውነትም ታግለውና አታግለው ያመጡት ስርአት ካጋጠመው ፈተና እንዲወጣ በማገዝ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ የሚል እምነት አለኝ።

በአሁኑ ወቅት እየተካሄደ ያለው የመልካም አስተዳደር ትግል አጠቃላይ ከሆነ አስተያየት ይልቅ እያንዳንዱ ባለሃብትና ዜጋ ያጋጠመው ችግር ፊት ለፊት እያቀረበ ችግሩ የራሱ ከሆነ ይብራራለታል አጥፊና ቀጣፊ ባለስልጣን ከተገኘ ህጋዊ እርምጃ እየተወሰደ ነው ያለው።በዚህ አጋጣሚ በቅርቡ በአንድ ከተማ የሆነውን ለአንባቢ በዚህ አጋጣሚ ልግለፅ (የከተማውና የተሻሚ ስም ያልተገለፀው በሂደት ላይ ስላለ ነው) ህዝቡ በከተማው ከተገነቡት ፕሮጀክቶች በተለይም በአንዱ ተገቢ ባልሆነ የጨረታ አካሄድ ተፈፅሟል ብሎ በማመኑና የክልል ሃላፊዎችም በማሳመኑ የተወሰደ እርምጃ ነው። እኚህ ከፍተኛ አመራር ያገኙት ከፍተኛ የትምህርት እድል በከተማው ካደረሱት በደል ጋር ተገቢነት የለውም የሚል የህዝቡ አስተያየት መሰረት በማድረግ ትምህርታቸው አቋርጠው ጉዳያቸው እንዲከታተሉ ህዝቡ በመጠየቁ ተግባራዊ እየተደረገ ነው። አይደለም ማስረጃ ተገኝቶበት መረጃ የተገኘበትም ቢሆን የህዝብ አስተያየት ብቻ በመውሰድ እርምጃ እየተወሰደ ነው ያለው። ከስልጣን የማውረድ፣ የማሸጋሸግ፣ ህግ ፊት በማቅረብ የተከናወኑ ተግባራት በየጊዜው በዓይጋ ላይ ስለተጫኑ ለጊዜው ልለፈው።

የተማሩና ሃብታም መሆን የፈለጉትስ ምን እየተደረገላቸው ነው? የሚል ጥያቄ አዘል አስተያየትም ተሰንዝሯል።

ክልሉ በየጊዜው እውቀት ገብይቶ በተለያየ ደረጃ የሚመረቅ ወጣት አቅሙ በፈቀደ መጠን ስራ እንዲፈጥር ለፈጠረው ስራ የስራ ቦታ፣ የብድር ድጋፍና የስልጠና ድጋፎች እየሰጠ ነው ያለው። በአሰራር አደረጃጀት ወዘተ የሚጎደል ነገር ካለ ሁሌም ውይይት እየተደረገበት ሰፊ መሻሻል መኖሩን ራሳቸው ተጠቃሚዎቹ እየመሰከሩበት ያለ ጉዳይ ነው። እስከ አሁን እንኳ 36 ሽሕ ኢንተርፕራይዞች የማቃቋምና ነባሮችን የማጠናከር ስራ ተሰርቷል። ይህ ቁጥር በአንድ ታዳጊ ኢኮኖሚ ውስጥ እጅግ ግዙፍ ነው ፍላጎቱ ከዚህ የላቀም ቢሆን። እነዚህ ተቋማት ለማቋቃምና ነባሮችን ለማጠናከር ከ830 ሚልዮን ብር በላይ ጠይቋል።ለአዳዲሶቹ ኢንተርፕራይዞች ከ992 ሄክታር መሬት በላይ ተሰጥቷል።

በአጠቃላይ አስተያየት ለማለፍ በተመኮረው ውስጥ ያለው የለውጥ ሂደት ሰገላለጥ ይህ ይመስላል። ከትሃድሶ በፊት ጨልሞ የነበረው የመላ ሀገራቱና የክልላችን ሁኔታ ካዛ ወቅት ጀምሮ የወረሳቸው የስርአቱ አደጋዎች የሆኑ በአቋራጭ የመበልፀግ ተግባሮችና ዝንባሌዎች እየታገለ የሚያጋጥሙት ፈተናዎች በፅናት ለማለፍ የሚያስችል ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ስርአት ተገንብቷል። እናም ችግሩ የስርአት ሳይሆን ስርአቱን በመገንባት ሂደት የሚያጋጥሙ ፈተናዎች በህዝባዊ ወገንተኝነት የመወጣትና ያለመወጣት ነው። ይህም በየግላችን ያሉን ተመሳሳይ ዝንባሌዎችና ተግባሮች በመታገልና ግልፅ መረጃና ማስረጃ በማቅረብ በአቋራጭ መበልፀግን ስንታገል እንጂ በአጠቃላይ አስተያየት ብቻ ማለፍ ትርጉም ይኖረዋል ብየ አላምንም። ሰላም።